# ያው ነገሠላችሁ!

ጥላሁን ገሠሠ
ጥላሁን ነገሠ

እንኳን ደስ አላችሁ ያው ነገሠላችሁ
ተነሳ ጥላሁን በቃ አመለጣችሁ
ከእንግዲህ የሱ ነው አገሩ ዘመኑ
እሱ ብቻ ይሆናል መዝሙሩ ዘፈኑ፤

ብያችሁ ነበረ በህይወት ይረክሳል
እንዳይሞት አደራ ከሞተ ይነግሣል፤

ብያችሁ ነበረ ተው አትግደሉት
ሞት ያነግሣልና አፍናችሁ ያዙት፤
ብያችሁ ነበረ ጣሉት የትም እርሱት
አይሙት አይኑር እንጂ አፈንፈን አድርጉት፤
ብያችሁ ነበረ አስርቡት አስጠሙት
መድረክ እዳያገኝ ስሙን እንዳይበላ
ውረሱት ዝናውን ግፈፉት ግርማውን፤

ሸንግሉት ስታዩት - ድንገት ስታነሱት
ከንፈር ምጠጡለት ውይ ጥልዬ! በሉት፤
ወዲያው ያምናችኋል ምንም አያውቅ እሱ
እንዴ ሰጥቷችኋል ፍቅሩን ከነነፍሱ፤

መክሬ ነበረ ጮሌ አይደለም እሱ፣ አያውቅም ገራም ነው
ዝምብሎ ኢትዮጵያ፣ ዝምብሎ አገር ነው፤
ሌላ ምንስ ያውቃል? አይተብትብ ነገር
ሌላ ምንስ ያውቃል? ከማዜም በስተቀር፤
ዝምብሎ ኢትዮጵያ ዝምብሎ አገር ነው
ሆድ ሳያውቅ ሆድ ብሶት ዝምብሎ ማልቀስ ነው፤

መክሬ ነበረ፣ ጮሌ አይደለም እሱ አያውቅም ገራም ነው፤
እንዳይሞት አባብሉት፣ እግሮቹን አሳስሩት
የት አባቱ ይሄዳል፣ እርፎ ይቀመጣል
በሐሜት ኮርኩሙት፣ ጩማ ስሙ ይመቻል፤
በሉት አጥፉት ድምጹን፤ በወረት ሰውሩት
አጠውልጉት መልኩን ቁመቱን ሸሽጉት፤

ከተልባው ከውጫጩ ዝለሉ ተንጫጩ፤
አያችሁ በለጠው! ንጉሡን አስናቀው!.. በማለት ለፍፉ
በወረት ደምስሱት - ጥላሁንን አጥፉ!
ዝለሉ ከውጫጩ ከተልባው ተንጫጩ
በቃኮ አለቀ! ተረሳ ደቀቀ! ብርጭቆ አጋጩ።

አውርዱት ከመድረክ ንሱት ግፉት ወዲያ
ወሽቁት ወትፉት፣ ይሰደድ አባሩት፣ ትምረረው ኢትዮጵያ
ይንከራተት የትም ይውጣ ይውረድ ይሂድ
ውረድ በሉት፣ ግፋ በሉት፣ ተቀምጠ ይንጎድ፤

ይዝለሉ ተረኞች ይምጡ ወጣቶቹ
ይበሉ- ሆሆ- ሆሄ- ያዮ - ያዬ- አያዬ- ቧቧዬ- ሆዬ- ቋቋዬ...
ይሸቅጡ ዜማ ይሸጡ ያሻሽጡ፤
ጥላሁን ይረሳ ይሁኑ ማስረሻ
ይሻላል የነሱ፣ ቢኖሩ ነው እንጂ ቢሞቱ አይገኑም
ይሻላል የነሱ፣ ሲኖሩ ነው እንጂ ሞተው አያስፈሩም፤

...እያልኩ ጨኬያለሁ እኔ ምን ቸገረኝ
በህይወት ይረክሳል ከሞተ ይነግሣል

ያልኩት መቼ ቀረ ይገናል ይኼ ሰው
የሞተ ይወዳል የኛ አገር የኛሰው፤
በቁሙ አልብሱት የመቃብርን አፈር
ብዬ ስነግራችሁ አልሰማ ብላችሁ
እግንዲህ አጨብጭቡ ያው ነገሠላችሁ፤

ፈንቅሎ አራግፎ አፈሩን ካላዩ
ከወጣ ጥላሁን ከታየው ሰማዩ
ፋሲካ ይሆናል ብድግ ይላል እሱ
ሞትን ያሸንፋል ይነግሣል ንግሡ፤
እሱም እንደጌታ ተነስቶ ከመጣ
አቤት ያለው ትዝብት አቤት ያለው ጣጣ!

መቸም አትሰሙኝ ያልኩት ሆነላችሁ
ጥላሁን ተነሳ እንኳን ደስ አላችሁ፤
በሉ አዘፍኑት ፈላልጉት ካሴቱን
-ኦ ጥላሁን! በሉ፣ ተርኩት ታሪኩን
እንደምስኪን ኑሮ እንደንጉሥ ሞቱን፤
ፍጠኑ ግጠሙ - ተራቀቁ እዘኑ
መቸም ታዛቢ አይኖር ጸጸትን ዝፈኑ፤

ቢሞት ወይስ ቢኖር? ብሎ የሚጠይቅ
አረፈን ከሞተ ቃል መርጦ የሚያስንቅ
ከተገኘባችሁ አንድ ሰው አንድ ሊቅ
እሱም ሰው ይነገሣል እንዳይሞት ጠብቁት
ሬሳ አድናቂ ባህልን እንዳይዘልፍ አድርጉት፤

ብቻ ምን ያደርጋል መቸም አትሰሙኝ
ቆሞ ያላየሁት ሲሞት ነገሠብኝ
እንግዲህ ላክብርህ ንጉሤ ጥላሁን
ወድጄም አይደለ - አንደኛ ነህ አሁን!

ደረጀ ደስታ
ኤፕሪል 22/2009